

ገድለ ቅዱስ ፊቅጦር

በግእዝና በአማረኛ



አሳታሚ
ማኅበረ ቅዱስ ፊቅጦር
ወአፍላጋተ ገዳማት ቅዱሳን አበው

ተጎትመ
ዝንቱ መጽሐፈ ገድል ፷፱ወ፫ ዓመተ ምሕረት

ሰማዕታቲሁሰ ለክርስቶስ

ይኽንን ርእሰ ቃል በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ የተናገረው ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ነው ። በደብረ ዘይት የጸመ ድጓ ነገረ ዜማ ውስጥ የምናገኘው መሉ ንባበ ዘርኡም <<...ሰማዕታቲሁሰ ለክርስቶስ አምጣነ ተሰዱ እምዝንቱ ዓለም ኃላፊ ወፈድፋደ ይትፌሥሑ ገሀደ በዓለም ዘይመጽእ...>> በማለት ተገልጿል ።

ትርጉሙም <<...ሰማዕታት ስለጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም የባሕርይ አምላክነት መሥክረው በዚኽ ኃላፊ ዓለም መከራን እየተቀበሉ ተሰድደዋልና በሚመጣው ሰማያዊ ዓለም እጅግ ደስ ተሰኝተው ይኖራሉ...>> በማለት የቅዱሳንን ክብረ ተጋድሎ የሚገልጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልዕክትን የሚያስተላልፍ ነው ።

ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም ስለአለፈው የቀደመ ግብሩ ሲገልጽ <<...ወአመሂ ቀተልኮ ለእስጢፋኖስ ሰማዕትከ-----የአንተን ነገር የሚያስተምር ሰማዕትህ እስጢፋኖስን በድንጋይ ወግረው ሲገድሉ በነገሩ ነበርኹበት...>> በማለት በጌታ ፊት የተናገረው ቃል ስለወልድ ዋህድ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብለው ፀዋትወ መከራን የተቀበሉ ቅዱሳን ኹሉ ሰማዕት ተብለው እንደሚጠሩ ይነግረናል ።

የሐዋ.ሥራ = ፳፪ ÷ ፳ ።

ሰማዕታቲሁሰ ለክርስቶስ ይኽንን ርእሰ ቃል በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ የተናገረው ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ነው ፡በደብረ ዘይት የጸመ ድጓ ነገረ ዜማ ውስጥ የምናገኘው መሉ ንባበ ዘርኡም <<...ሰማዕታቲሁሰ ለክርስቶስ አምጣነ ተሰዱ እምዝንቱ ዓለም ኃላፊ ወፈድፋደ ይትፌሥሑ ገሀደ በዓለም ዘይመጽእ...>> በማለት ተገልጿል

ትርጉሙም <<...ሰማዕታት ስለጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም የባሕርይ አምላክነት መሥክረው በዚኽ ኃላፊ ዓለም መከራን እየተቀበሉ ተሰድደዋልና በሚመጣው ሰማያዊ ዓለም እጅግ ደስ ተሰኝተው ይኖራሉ...>> በማለት የቅዱሳንን ክብረ ተጋድሎ የሚገለጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልዕክትን የሚያስተላልፍ ነው ::

ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም ስለአለፈው የቀደመ ግብሩ ሲገልጽ <<...ወአመሂ ቀተልዎ ለእስጢፋኖስ ሰማዕትከ-----የአንተን ነገር የሚያስተምር ሰማዕትህ እስጢፋኖስን በድንጋይ ወግረው ሲገድሉ በነገሩ ነበርኹበት...>> በማለት በጌታ ፊት የተናገረው ቃል ስለወልድ ዋህድ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብለው ፀዋትወ መከራን የተቀበሉ ቅዱሳን ኹሉ ሰማዕት ተብለው እንደሚጠሩ ይነግረናል ::

የሐዋ.ሥራ = ፳፪ ÷ ፳ ::

እንገዲህ ወንጌላዊ ተልዕኮ ተጋድሎውን በሰማዕትነት የፈጸመ ይኽ ቅዱስ ጳውሎስ በሌላው ክፍለ መልዕክቱ "...እሙን ነገር እምከመ ዐረይነ መዊተ ንዴሪ ሕይወተ---የእርሱን ሞት ከተካፈልን ከእርሱ ጋራ በሕይወት እንኖራለን ..." ይላል::

እኛም የእነርሱን አሠር ተከትለን በዓለም ዐደባባይ ፊት በእምነታችን ጸንተን ቆመን ሰማያዊ ሕይወትን እንወርስ ዘንድ "በሰማይ እግዚአብሔርን እንደ ሚያገለግሉ መላዕክት ኾነው የሚኖሩ የእኒኽ ቅዱሳን ሰማዕታት አማላጅነታቸው ይጠብቀናል ያጸናናል ::

ዕብ = ፲፪ ÷ ፩ :: ፪ ጢሞ = ፪ ÷ ፲፩ ::

ስለዚህም ነው <<...አቤቱ እውነተኛ የባሕርይ አምላክ ሆይ ደማችንን በማፍ የአፈሰሱትን ሰዎች በምድር ከሚኖሩ ሰዎች ለይተህ አትፈርድልምን...>> በማለት እኒህ ቅዱሳን ሰማዕታት በዐፀደ ነፍስ እያሉ በዐፀደ ሥጋ ለምንኖር ለእኛ የሚማልዱልን ::

ራእ = ፮ ÷ ፲፪ :: ማቴ = ፳፪ ÷ ፳፯ :: ዕብ = ፮ ÷ ፲፪ ::

ከላይ እንደተገለጸው ቅዱሳን ሰማዕታት ልዩ ልዩ ፀዋትወ መከራን ተቀብለው ይህንን ዓለም ድል ይነሡ ዘንድ በሕያው የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተመረጡ ሕያዋን ናቸውና በአካለ ነፍስም በአካለ ሥጋም የአምላካቸው ልዑል እግዚአብሔር ገቢረ ተዐምራት የሚገለጽባቸው በተጋድሏቸው ከዓለሙ ክበደ ፈተና ትእግሥትን የምንማርባቸው አማላጆቻችን ናቸው ::

ነቢይ ኤልሣዕን እንመልከት :: የተቀደሰ አካለ ሥጋው በዐረፈበት መቃብሩ ቀባሪዎች የተሸከሙትን የመዋቲ አካለ በድን በድንገት በአኖሩ ጊዜ ሙት የነበረው ሰው በነቢይ ኤልሣዕ አማላጅነት በሕይወት ተነሥቶ አዲስ ሕይወት ሰጥቶ ከሞት የአነሣው አምላኩ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን አመስግኗል ::

፪ ነገ = ፲፫ ÷ ፳ :: ማር = ፲፪ ÷ ፳፯ ::

በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልም ቅዱሳን ኹሉ ዓለሙን ወደአስገኘው ፈጣሪያቸው በማማለድ ምሕረትን ከማሰጠትም በላይ በዓለሙ ኹሉ ላይ ፈራጆችና ዳኞች ኾነው እንደተሾሙ "...በዐሥራ ኹለቱ ነገደ እስራኤል ልትፈርዱ በዐሥራ ኹለቱ ዙፋን ትቀመጣላችሁ..." ያለውንና "... ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ አታውቁምን..." በማለት ያቀረበውን መጠይቃዊ ማስረጃ መመልከት ያስፈልጋል ::

ማቴ = ፲፱ ÷ ፳፰ :: ፩ ቆሮ = ፮ ÷ ፪ ::

በዓለም ላይ እንዲፈርዱ ብቻ አይደለም ። እርሱ ባለቤቱ የሠራዊት ጌታ አምላካችን እግዚአብሔር በዐወቀ ለወዳጆቹ ቅዱሳን የሰጣቸው ሌላም ትንቢታዊ ዕዳ አለ ። እውነት ነው ። የእርሱ ቸርነታዊ ጸጋ እጅግ ብዙ ነው ።

ቅዱስ መጽሐፍም ይኸንኑ ሲያረጋግጥ "...ወብክሙ ጸጋ እግዚአብሔር--------ከአምላካችሁ እግዚአብሔር የተሰጣችሁ ልዩ ልዩ ጸጋ አላችሁ..." ይላል ። ከእነዚኽም ጸጋዎች አንዱ ሀብተ ትንቢት ለሰማዕቱ ቅዱስ ፊቅጦር ተሰጥቶት ከአንያኪያ እስከ እለእስክንድርያ ምድር ይልቁንም ባርቆን ድረስ በስደት ተግዞ በተቀበለው ፀዋትወ መከራ ውስጥ ሳለ በዚኽ የመጨረሻው ዘመን ስለሚከሠተውና ስለሚኾነው ነገር ኹሉ ግልጥ ትንቢትን ተናግሯል ።

ሮሜ = ፲፪ ÷ ፮ ።

ይኸን ትንቢቱንም በዚኹ መጽሐፈ ገድል ውስጥ እንደምና ነበው በዚኽ በአለንበት ዘመን እየታየ ያለውን አስከፊና አስደንጋጭ የጭንቅ ኩነትና በመጨረሻም መልካም ዘመን እንደሚመጣ ደግ ንጉሥ ቴዎድሮስ እንደሚነሣ ይናገራል ። በተጨማሪም "...በዚያ ዘመን ሰዎች እርስ በእርሳቸው ይጠላላሉ ። አንዱ አንዱን ለሞት አሳልፎ ይሰጠዋል ይገድለዋል ። ሐሰተኞች ነቢያትና ሐሰተኞች መምህራን ይነሣሉ ፡ ብዙ ሰዎችን ያስታሉ ። ከሐሰትና ከኃጢአት ብዛት የተነሣ ፍቅር ትመነምናለች ።

በዚያ ዘመንም ብዙዎች ሃይማኖታቸውን ይክዳሉ ።ምግባራቸውን ይለውጣሉ ። በዓለም ኹሉ መከራ ይኾናል ። የታገሠበቻ እርሱ ይድናል...." ይላል ።

እነሆ ይኸንንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የአብነት ትምህርታት አንዱ ኾኖ የሚሰጠውና ከ1957 ዓመተ ምሕረት ጀምሮ የታተመው የአንድምታ ትርጓሜ ወንጌል በ165ተኛ ገጹ ላይ ይኸንኑ ሲያረጋግጥ "...ወይሰበክ ዝ ወንጌሰ መንግሥት ውስተ ዅሉ ዓለም..." ማለትም "...ወንጌል በአራቱ ማዕዘን ትነገራለች ። በአሕዛብ ቤት ላይቀር ትገኛለች..." ካለ በኋላ በዚኽ የትርጓሜ ወንጌል ሐተታ ውስጥ <<...በሀገራችን ቴምድሮስ ፤ በሀገራቸው ሮም ዮሐንስ የሚባል ይነግሣል ። የእኛም ሐዲ ያም መጥቶ በእስክንድርያ ሦስት ቀን ይዋጋሉ ። አራቱ ሊቃነ ጳጳሳትም " የክርስቲያን ደም ለምን ይፈስሳል ። መሥዋዕትን ሠውተን ፤ በመሥዋዕቱ ምልክት በታየለት ሃይማኖት ይጽና ይሏቸዋል ። ኾሉም በእያሉበት መሥዋዕት ያቀርባሉ..... ... የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት በሠዋው መሥዋዕት ላይም 'እነ ውእቱ ክርስቶስ ' ብሎ በርግብ አምሳል ወርዶ ይመሠክራል ።

ከዚኽ በኋላ በሃይማኖት አንድ ይኾናሉ ። እንደዚህ የሚል ከምን አለ ቢሉ ከገድለ ፊቅጦር ከገድለ ሲኖዳ ይገኛል...>> የሚል አማናዊ የሐተታ ታሪክ በዚኽ የጉባኤ ትምህርት ውስጥ ተጽፎ ይገኛል ። እንግዲህ በልዩ ልዩ ዓለማትና በሀገራችንም የሚታዩትን የሰላም መጥፋት ፤ የፍቅር መመንመን ፤ ሃይማኖትን መለወጥ በምግባር መዝቀጥ የጉቦና የሌብነት የጥላቻና የዘረኝነት ኃጢአት መበርከትንና የመሳሰሉትን ጥላቻዎችና ሽብሮችን ስንመለከት እኒኽ ኹሉ ከመድረሳቸው አስቀድሞ በሰማዕቱ ቅዱስ ፊቅጦር የተነገረው ትንቢት በዘመናችን እየተፈጸመ መኾኑን እንረዳለን።

እንግዲህ የአንበሳ ደቦል ስለተሰኘው ደግ ንጉሥ ቴምድሮስ መምጣት ቅዱስ ፊቅጦር የተናገረውን ሙሉ ትንቢት የያዘው ይኽ መጽሐፈ ገድለ ቅዱስ ፊቅጦር በዘመናችን ከልሳነ ግእዝ ወደአማረኛ

ተተርጕሞ መቅረቡ በሰማዕቱ ቅዱስ ፊቅጦር ትንቢትም ጭምር የዘመናችን መጨረሻ ኩነት ለመላው ዓለም ይገለጽ ዘንድ ፈቃደ እግዚአብሔር ቢኾን ነው ::


ስለዚኽም በመግቢያችን ርእሰ ቃል መሪነት እንደተገለጸው በሚመጣው ሰማያዊ ዓለም ደስ ተሰኝተውና ዘለዓለማዊ የድል አክሊልንም ተቀዳጅተው ይኖሩ ዘንድ ከተመረጡ ሰማዕታተ ክርስቶስ አንዱ የኾነው ቅዱስ ፊቅጦር ከአምላኩ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በተሰጠው የትንቢት ጸጋ አሁን የምንገኝበትን የመጨረሻውን ዘመን መከራውንና ተስፋውን አስቀድሞ የአመላከተን ኹላችን ለንሥሓ ሞት ለርስተ ገነት እንበቃ ዘንድ አስቀድመን እንድንዘጋጅ ነውና ለደገኛው ንጉሥ ደገኛ ዘመን እንድንበቃና ይኽንን በመንፈሰ ትንቢት የከበረ መጽሐፈ ገድል በሚገባ በማስተዋል እንጸልይበት ዘንድ ታላቁ ሰማዕት ንዑድ ክቡር ቅዱስ ፊቅጦር በአማላጅነቱ ይርዳን አሜን።

ተርጓሚ


ሊቀ ጉባኤ ቀሲስ ታረቀኝ ብርሃኑ

የቅኔና የትርጓሜ መምህር

09 11 64 23 36



ዘከመ ተቃተለ ቅዱስ ፊቅጦር ሰማዕት ምስለ አሕዛብ ነገሥት ወዐላውያን መኳንንት



አንድ አምላክ በሚኾን በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም አምነን የሰማዕት ቅዱስ ፊቅጦርን በተባረከ መርኃ ሐምሌ የሚ ጸለይ መጽሐፈ ገድሉን እንጀምራለን ። ጸሎቱና በረከቱ ክ.....ጋራ ይኹን በእየጊዜውና በእየሰዓቱ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን።

፩. እናቱ ቅድስት ማርታም በመንፈቀ ሌሊት ተኝታ ሳለች ልጇ ቅዱስ ፊቅጦር ተገልጦ እናቱ ማርታ ሆይ ሰላም ከአንቺ ጋራ ይኹን ። አስተውይ በሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ማዕዘናት ላይ ወርቅንና ብርን አታድርጊ አሕዛብ የሚነሡበት ዘመን አለና እነርሱም በእየማዕዘናቱ የአለውን ወርቁንና ብሩን በአዩ ጊዜ ይሸቺን ቤተ ክርስቲያን ወርቁን ለማግኘት ብለው ያፈርሷታልና አንቺ ግን በድንጋዮችና በብረት በዕንጨቶችም ሥሪ ። የቤተ ክርስቲያኒቱም ሕንፃ ረኻቦም ዘመን ትኖራለች ።

፪. እናቱ ቅድስት ማርታም አሕዛብ በግብፅ እንደ ሚነግሡ በሰማች ጊዜ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ብላ እጅግ አዘነች ልጁ እንደዚህስ ከኾነ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንን ለማነፅ ስለምን እደክማለሁ አለችው ልጇ ንዑድ ክቡር ሰማዕት ቅዱስ ፊቅጦርም እናቱ ሆይ አሕዛብ ቢመጡም አምልኩተ ክርስቶስ በግብፅ አውራጃዎች ኹሉ እምነትና ጸም ጸሎትና ቍርባን ይኖራል እንጂ አይታጐልም ከከሃዲዎች አሕዛብ ጋራ ሲኖር እኮ ጽንዐ ሃይማኖት ይጸናል በመንበረ ማርቆስም የሊቀ ጳጳ ሳት መሾም በሊቀጳጳሳትም እጅ የጳጳሳትና የኤጲስቆጶሳት የቀሳ ውስትና የዲያቆናትም በእየማዕርጋቸው መሾም አይቈረጥም ።

፫. መመንግሥተ ተንባላትስ ጎዳጥ መዋዕል እመንቱ እምእለ ይገብሩ ክርስቲያን ፈቃደ እግዚአብሔር ። ወእምድኅረ ጎዳጥ መዋዕል ያነግሥ እግዚአብሔር ላዕለ አህጉረ ኢትዮጵያ ንጉሥ ብእሴ ቅዱስ መፍቀሬ እግዚአብሔር ዘስሙ ቴዎድሮስ ወበእደ ዚአሁ ይትነሠቱ ተንባላት ወአረማውያን ። ወይገርሩ ሎቱ ነገሥተ አሕዛብ ወግብጻ ውያን ። ወይትንብኡ ውስተ አብያቲሆሙ ። ወኢያስተ ርእዩ እስከ ተፍጻሜተ ዓመት ። ወሊቀ ጳጳሳት ይሰየም ወይት ኀላእ ውስተ በአታ ለኅብእት ደብር ። ወይጼሊ ኀበ አምላኩ እግዚአብሔር በእንተ ሕዝቡ ። ወይሰምዕ አምላክ ለእለቶ ።

፬. ወይበጽሕ ኀቤሁ መኰንነ ሠራዊት እምኀበ ንጉሥ ኢትዮጵያ ። ወይጼውዖ ወይነግሥ ውእቱ ላዕለ ብሔረ ግብጽ ፲ወ፩ አውራጎ ወይሄሉ በሰላም ወበዐቢይ ፍሥሓ ። ወእምዝ ካዕበ ይሰምዕ ንጉሥ ሮሜ ይመልዕ መዓተ ወቅንዐተ ። ወይጽ ሕፍ ኀበ አብያዊሁ ነገሥተ ዓለም ። ወይነሥእ ምስሌሁ ነገሥተ ወየሐውር እስከ ኀበ ኢየሩሳሌም ።

፭. ወሶበ ሰምዐ መኰንነ ንጉሥ ኢትዮጵያ ወይጐይይ ምስለ ሠራዊቱ ወይበጽሕ ኀበ ላዕላይ ግብጽ ። ወይልዕክ ኀበ ንጉሥ ኢትዮጵያ እንዘ ያጤይቆ ግብረ ዘኮነ ። ወሶበ ይሰምዕ ንጉሥ ኢትዮጵያ ይመልዕ መዓተ ። ወይመጽእ ኀበ ምድረ ግብጽ ። ይመዘብራ ወይነግሥ ላዕሌሃ ። ወይፈኑ ሊቀ ጳጳሳቲሁ ኀበ ንጉሥ ሮም ወካልዓነ ምስሌሁ እምነ ዐበይቱ ። ወሶበ የሐውሩ እመንቱ ካዕበ ውእቶሙኒ ይፈንው ሊቀ ጳጳሳቲሆሙ ። ወይነብሩ ውስተ መካን ጉቡኣነ ዅሉሙ ወይትሐተቱ በበይናቲሆሙ በእንተ ርትዕት ሃይማኖት ።

፫. ፈቃደ እግዚአብሔርን ከሚጠብቁ ክርስቲያን የተነሣ የአሕዛብ መንግሥትም የሚቆይ ጥቂት ዓመት ነው ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር አምላክ በኢትዮጵያ ግዛቶች ሹሉ እግዚአብሔርን የሚወድድ ቅዱስ ሰው ስሙ ቴዎድሮስ የተሰኘ ንጉሥንን ያነግሣል ። በእርሱ እጅም አሕዛብና አረማውያን ይጠፋሉ የአሕዛብና የግብግውያን ነገሥት በእየመኖሪያቸው ተሸሽገው ይገዙለ ታል ። እስከ ዘመኑ መጨረሻ አይገዳደሩትም ከተሠወረች ደብር ተሸሽጎ ሲኖር የተሾመ ሊቀ ጳጳሳትም ስለሕዝቡ ወደአምላኩ እግዚአብሔር ይለምናል ። አምላኩም ልመናውን ይሰማዋል ።

፬. ከኢትዮጵያ ንጉሥ ዘንድ የተላከ የጦር ሠራዊት አለቃም ይመጣል ተቀብቶ ነግሦም በግብጽ ግዛቶች ዐሥራ አንድ ወራቶች በሰላምና በታላቅ ፀጥታ ይገዛል ። ከዚያ በኋላም የሮም ንጉሥ ሰምቶ በቁጣና በቅንዐት ይነሣል ። ወደመሰሎቹ የዓለም ነገሥት ደብዳቤን ይጽፋል ። ከራሱም ጋራ ሌሎች ነገሥትንም ጨምሮ ወደ ኢየሩሳሌም ይዘምታል ።

፭. በንጉሥ ኢትዮጵያ የተሾመው ገዥም ሰምቶ ከእነሠ ራዊቱ ወደላይኛው ግብጽ ይሸሻል ። የኾነውንም ነገር ለኢትዮጵያ ንጉሥ ይነግረዋል ። የኢትዮጵያ ንጉሥ ሲሰማም በቀጣ ተመልቶ ወደምድረ ግብጽ መጥቶ ይወርራታል ። በላይዋም ይነግሣል ። ሊቀ ጳጳሳቱንና ከእርሱም ጋራ ከሹማም ንቱ መኻል ወደሮም ንጉሥ ዘንድ ይልካል ። እነርሱም በሔዱ ጊዜ እነዚያም ሊቀ ጳጳሳቸውን ይልካሉ ። ኹላቸውም በአንድ ቦታ ተሰብስበው ስለቀናችቱ ሃይማኖት እርስ በእርሳቸው ይጠያየቃሉ ።

፮. ወእምድኅረ ተሳትፎተ ዓመት ይብል ለቀ ጳጳሳተ ኢትዮጵያ ለሊቀ ጳጳስተ ሮም ነአ ንሑር ከመ ናብዕል ውስተ ኢየሩሳሌም ንሕነ ክልኤነ ምስለ ሰብዐቱ ነገሥትነ ወኩሉ ሰሰአሀዱ እምኔነ ይቁም ወይጸሊ ውስተ መነነ ቤተ ክርስቲያን ወሶቡ ሰብእ እንዘ ይፌኢ ገሃደ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እንዘ ይወርድ እምሰማይ ዲበ ቍርባኑ ርትዕት ሃይማኖቱ ። ወከመዝ የኀብሩ ነገሥት ወሊቃነ ጳጳሳት ። ወይትነሥኡ ወይመጽኡ ኀበ ኢየሩሳሌም ፡ ወይበውኡ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ። ወያዐርጉ በበመትልዉ ቍርባነ በህየ ።

፯. ወእምድኅረ አንብቦተ መንጌል ይፌኢ ኵሉ ሰብአ ገሀደ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እንዘ ይወርድ ላዕለ ቍርባኑ ለሊቀ ጳጳሳት ዘእለ እስክንድርያ ። መሶበ ይፌእዩ ርምሀ ዘንተ ይፈርሑ ፈድፋደ ወየኀዝኑ ወይትሀውኩ ። ወይነሥኡ መሥዋዕቶሙ እምላዕለ ማዕዳቲሆሙ ። ወይዌርውም ውስተ ባሕር ። ወያውዕ ይምሙ ለመጻሕፍቲሆሙ በእሳት ይብሉ በሀከት አሌ ለነ እስመ ኃጢአት ተሠልጠት ለዕሌነ ። ወባሕቱ ኢኮነ ዝንቱ በእንተ ኃጢአትነ አላ በእንተ ኃጢአት እንተ ገብርዋ አበዊነ በድፍረቶሙ ዕኪት ።

፰. ወበይእቲ ሰዓት ያደንኑ ወይሰግዱ ለሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወይብልዎ ባርክ ላዕሌነ አ አቡነ ። ወይኤምኑ ክልኤቱ ነገሥት በበይናቲሆሙ ወይትሳየዱ ። ወየኀድግ ንጉሠ ሮሜ ውስተ ምድረ ግብጽ ወልድ እኑሁ ። ወንጉሠ ኢትዮጵያኒ የኀድግ ለመሁ ። ወይገብኡ ለለብሔሮሙ በእማን ። አ እምየ ዐቢይ ፍሥሓ ይከውን ለዝሉ ሰብእ በውእቱ መዋዕል እስከ ይቀውመ ሕያዋን ላዕለ ምውታን ። ወይብልዎሙ ተንሥኡኬ ከመ

፮. በዓመቱ መፀኤረሻ ላይም የኢትዮጵያው ሊቀ ጳጳሳት የሮሙን ሊቀ ጳጳሳት ና እኛ ዝሉታችን ከሰባቱ ሹማምንት ራሶ ቻችን ጋራ ወደኢየሩሳሌም እንሒድ ። ዝሉም እየአንድ አንዱ በቤተ ክርስቲያን ቁሞ ይጸልይ ። ዝሉም ሰው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ከሰማይ በቀርባኑ ሲወርድ የተገለጸለት ሃይማኖቱ የቀናች እውነተኛ ናት ማለት ነው ይሰዋል ። ነገሥታቱና ሊቃነ ጳጳሳቱእንዲህ ተነጋግረው ተነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ይሔዳሉ ። ወደ ቤተ ክርስቲያንም ወስጥ ገብተው በዚያ መሥዋዕተ ቀርባን በእየተራ ያቀርባሉ ።

፯. ወንጌል ከተነበበ በኋላም የእለ እስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት በአቀረበው መሥዋዕተ ቀርባን ላይ ዝሉም ሰው በግ ልጥ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ ያያል ። ሮማውያን ይሽንን አይተው እጅግ ፈርተው ያዝናሉ ይተክዛሉ ። መሥዋዕታቸ ውንም ከመንበሩ ላይ አንሥተው ወደዐዘቅት ይወረውራሉ ። ኃጢአት በእኛ ላይ ሠልጥኖብናለችና ወዮልን ። ወዮታ ይገባናል ነገር ግን አባቶቻችን በክፉ ድፍረታቸው ስለሠሯት ኃጢአት ነው እንጂ ይሽ የሽነ በእኛስ አይደለም እያሉ መጻሕፍቶቻቸውን በእሳት ያቃጥላሉ ።

፰. በዚያች ሰዓትም ለኢትዮጵያው ሊቀ ጳጳሳት እየሰገዱ አባታችን ሆይ አባከህ ባርከን ይሉታል ። ዝሉቱም ነገሥት እርስ በእርሳቸው ይስማማሉ ። የሮም ንጉሥ በግብጽ የወንድ ሙን ልጅ ። የኢትዮጵያም ንጉሥ አማቹን በገብፅ ሾሞ በሰላም ወደእየሀገራቸው ይመለሳሉ ። እናቱ ሆይ በዚያን ዘመን ሕያዋን በሙታን መቃብር ላይ ቁመው እግዚአብሔር የአደረገልንን ይሽንን ታላቅ ደስታና ጸጋ ብዙ በጎ ስጦታዎችን ታዩ ዘንድ

ትርአዩ ዘንተ ዐቢያ ኍንግዓ ወጸጋተ ወብዙኃተ ሠናያተ እንተ ገብረ ለነ እግዚአብሔር ። ወበውእቱ መዋዕል ይከውኑ ኵሉ ሰብእ ግባርያነ ፈቃደ እግዚአብሔር ። ወያቲመረዐው ንጉሠ ኢትዮጵያ ወለተ ንጉሠ ዮናናውያን ዘውእቱ አኍሪንጋ ውያን ወይከውን አሜሃ ኍሥሓ ወሰላም ውስተ ኵሉ ዓለም ፸ ዓመተ ወይገብር እግዚአብሔር ልዑል ምሕረቶ ላዕለ ሕዝቡ ።

፱. ወእምቅድመ አማንቱ መዋዕል ይትነሥኡ ክልዔሆመ ንጉሠ ኢትዮጵያ ትዮዳ ወንጉሠ ሮም ። ወይትጋብኡ በዝ መነን ለሰብዐቱ ዓመታት ምስለ ሊቃነ ጳጳሳቲሆመ ወምስለ ሠራዊቶመ ወምስለ ኵሉ ሕዝብ ። ወበከመ አቅደምኩ ነገረ ይወርድ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ቍርባኖመ ለኢትዮጵያ እለ ይትአመንዎ ። ወይብሉ ሕዝብ ብዑዕ ውእቱ ዝ ነገር ። አይሁድኒ ወተንባላትኒ ወአረሚኒ ይከውኑ ክርስቲያነ ።

፲. ወይቀውም ኵሉ ዓለም በሃይማኖተ ኢትዮጵያ ። ወሮምሰ የዐወይዉ ወይዌርዉ መጻሕፍቲሆመ ውስተ ባሕር ወይጠመቁ ሮምኒ ወተንባላትኒ ወአይሁድኒ ወአረሚኒ ኵሎመ ኀቡረ ። በስመ ሥላሴ ቅድስት ።

፲፩ ወይጸርሕ ዐዋዲ ሐሩ ወስብኩ ለአዝማዲክመ ወለአይሁድ አይሁድኒ ለአይሁድ ወተንባላት ለተንባላት ወአረማውያን ለአረማውያን ። ወለዘአበየሰ አሚነ ወሰጊደ ትትሐበዮ ሰይፍ ይእተ አሚረ በስመ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

፲፪. ወከመዝ ትዕምርቱ ለውእቱ ንጉሥ ላህይ ወጸሓም ወይስዕሮ ለንጉሠ ምስር (ግብፅ) ወይሠይም ህየንቱሁ ካልዐ ። ወውእቱ

ተነሡ አስከሚሉ ድረስ ታላት ደስታ ይኾናል ። በዚያን ዘመንም ሰዎች ኹሉ ፊቃደ እግዚአብሔርን የሚፈጽሙ ደጋግ ሰዎች ይኾናሉ ። የኢትጵያ ንጉሥም አፍሪንጂያውያን የኾኑ የዮናና ውያንን ልጅ ያገባል ። ያን ጊዜም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ቸርነቱን አብዝቶ ያደርጋልና በዓለም ውስጥ ለአርባ ዘመን ፍሥሓና ሰላም ይኾናል ።

፱. ከነዚያ ቀኖች በፊት ግን የኢትዮጵያ ንጉሥ ትዮዳና የሮም ንጉሥ ይነሣሉ ። በዚህም ቦታ ከሊቃነ ጳጳሳቶቻቸውና ከሠራዊታቸው ከሕዝባቸውም ጋራ ለሰባት ወራትም ሕገ ሃይማኖትን እየወሰኑ ይቀያሉ ። አስቀድሜ እንደተናገርሁም በሚታመኑ ኢትዮጵያውያን ቊርባን ላይ መንፈስ ቅዱስ ይወር ዳል ሕዝቡም ይኽ ነገር ንዑድ ክቡር ነው ይላሉ ። አይሁ ድና እስራኤል አሕዛብም ክርስትናን ይቀበላሉ ።

፲. ዓለም ኹሉ በኢትዮጵያ እምነት ይጸናል ። ሮማ ውያን ግን በዋይታ እየተቊጡ መጻሕፍቶቻቸውን ኹሉ ወደ ባሕር ይወረውራሉ ኹላቸው ሮማውያንና ዐረቦች አይሁድና አረማውያንም በቅድስት ሥላሴ ስም አምነው ይጠመቃሉ ።

፲፩. ዐዋጅ ነጋሪም ሐዲሱ ኹላችሁም ለዘመዶቻችሁ አይሁድም ለአይሁድ እስላሞችም ለእስላሞች አሕዛብም ለአሕ ዛብ አስተምሩ እያለ ይጮኻል ። ያን ጊዜም በጌታችንና በአምላ ካችን በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምኖ ያልሰገ ደውን ሰይፍ ታጠፊዋለች ።

፲፪. የዚያ የኢትዮጵያ ንጉሥ ምልክቱ ደም ግባቱ ያማረ ጢማም ነው ። የምስርን (የግብፅን) ንጉሥ ሸሮ ሌላ ይሾማል ።

ንጉሠ ኢትዮጵያ ይመይጦን ለግዮን ወለማየ ተክዜ ከመ ይንሣእ ጸባሕተ እምግብዕ ። ወንጉሠ ሮሜ ይመልካ ለኢየሩሳሌም ፡ ወከመዝ ትዕምርቱ ለውእቱ ንጉሥ ላህይ በርእየቱ ወነዊኅ ቆመ ዘቦቱ ትዕምርተ መስቀል ማዕከለ አጥባቲሁ ።

፲፫. ወበውእቱ መዋዕል ይትአሰሩ አጋንንት መጠነ አርብዓ ዓመት ፡ ወይከውን ዛነን ፍሥሓ ወሰላም ውስተ ኵሉ ዓለም ለውእቱ አርብዓ ዓም ። ወእምብዝኃ ሰላም ይዘንም ዝናመ በረከት ዘእንበለ ደመና ሰባተ ዕለታተ ። ወበውእቱ መዋዕል ኵሉ ሰብእ ይከውን ለገነተ እግዚአብሔር ድልወ ። ወለነኒ ይክፍለነ ምስሌሆሙ አሜን ።

፲፬. ወዘይመውትሂ በውእቱ መዋዕል ይፈልስ ዘእንበለ ፃማ ማዕቀፌ ጌጋዩ እስመ ተስዕረ ኵሉ ኀጢአት ወኵሉ ዐመፃወአልቦ ፀብዕ ወባዕስ ዘእንበለ ጸም ወጸሎት ወፍሥሓ ወሐሤት ወአልቦ ኀጡአ ። ወእምዝ ይነግሡ ፯ ነገሥት ዘስሞሙ ፩ አ ።
፪ ሮ ። ፫ ወ ። ፬ ፊ ። ፭ ማ ። ፮ ዮ ። ፯ ሐ ።

፲፭. ወአመ ይወርድ ንጉሠ ኢትዮጵያ ውስተ ኢየሩሳ ሌም ወይነግድ ንጉሠ ሮምኒ እምቍስጥንጥንያ ። ወየሐውር ንጉሠ ኢትዮጵያ ምስለ ሊቀ ጳጳሳት ዘአለእስክንድርያ ። ወይመጽእ ንጉሠ ሮምኒ ምስለ ሊቀ ጳጳሳት ዘቍስጥንጥንያ ። ወይትረከቡ ውስተ ቤተ ክርስቲያኑ ለአቡነ ቅዱስ አባ ሲኖዳ ጸድቅ ብእሴ እግዚአብሔር

የኢትዮጵያው ንጉሥ ከግብፅ ግብርን ይቀበል ዘንድ ወራጁን የመሪን ውኃንና የተከዜን መንዝ ይገድባል ። የሮሙ ንጉሥም ኢየሩሳሌምን ይጣታል ። የዚያ ሰው ምልክቱም በጡቶቹ መኻል ትዕምርተ መስቀል ያለው መልኩ የሚያምር ቁመቱ ረዥም ነው

፲፫. በዚያን ዘመን አጋንንት ይታሰራሉ ። ምድሪቱም ለአርባ ዓመት ያህል ታርፋለች ። በአራቱ ማዕዘን ወጥታና ደስታ ፍቅርም ይበዛል ። ፍቅር ፣ አንድነት ከመብዛቱ የተነሣም የበረከት ዝናም ያለደመና ሰባት ቀን ይዘንማል ። ያን ጊዜ ሰው ኹሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ የተዘጋጀ ይኾናል እኛንም ከእነርሱ ጋር ያድለን አሜን ።

፲፬. በዚያን ጊዜ የሚሞት ሰው ኹሉ ያለ ድካም ይሻገ ራል። በደልና ኃጢአት ኹሉ ጠፍተዋልና ከጾም ከጸሎት ከደስታና ከሐሤት በቀር ጠብ ክርክር አይኖርም ። የሚታጣ ነገርም የለም ። ከዚህ በኋላ ስማቸው የፅኛው አ የፀኛው ሮ የቨኛው ወ የፀኛው ፊ የሯኛው ማ የሄኛው ዮ የሂኛው ሐ የሚለኝ ፯ ነገሥታት ይነግሣሉ ።

፲፭. የኢትዮጵያ ንጉሥ ወደ ኢየሩሳሌም በሐዲ ጊዜ የሮሜም ንጉሥ ወደ ቍስጥንጥንያ ይሐዳል ። የኢትዮጵያም ንጉሥ ከእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ጋራ በሐዲ ጊዜ የሮሜም ንጉሥ ከቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት ጋራ ወደ እስክንድሮያ ይመጣል በእግዚአብሔር ሰው ጻድቁ ቅዱስ አቡነ አባ ሲኖዳ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገኛሉ ።

፲፯. ወይብል ንጉሠ ሮሜ ምስለ ሊቀ ጳጳሳት ዘቍስጥን ጥንያ ዘዚአነ ሃይማኖት ይኔይስ ። ወይብል ካዕበ ንጉሠ ኢትዮጵያ ምስለ ሊቀ ጳጳሳት ዘእለእስክንድርያ እንቲአነ ሃይማ ኖት ትኔይስ ወትሜኒ አንትሙሰ ሰብአ ሮሜ ገበርክሙ ፍልጠተ ማዕከለ ትስብእቱ ወመለኮቱ ። ወከፈልክምዎ ለዘኢይ ትከፈል ። ወአንቃዕክምዎ ለዘኢይትሌለይ ። ወአምዝ ይነውኅ ጋዕዝ በእንተ ተስናነ ነገርኒ ወበቃለ መጻሕፍትኒ ።

፲፰. ወትውፊተ መጻሕፍቲሆሙኒ ለኢትዮጵያውያን ዘብ ሉይ ኮነ አመ ፀአታ ለንግሥተ አዜብ እምኢየሩሳሌም ። ወትው ፊተ መጻሕፍቲሆሙ ዘሐዲስ ኮነ አመ ፀአቶሙ ለተስዐቱ ቅዱሳን ዘሮሜ ። ወአምዝ ይመውዕምሙ ሊቃውንተ ኢትዮጵያ ለመምህራኒ ሮም እስመ መጻሕፍቲሆሙ ኀየለ እመጻሕፍተ ኵሉ ዓለም በከመ ይቤ ነቢይ ኢሳይያስ አሌ ሎን ለአሕማር እለ ቦን ክንፍ ውስተ አፍላገ ኢትዮጵያ ።ወይፈኑ ውስተ ባሕር ወያመጽኡ መጻሕፍተ ።

ኢሳ = ፲፰ ፥ ፪

፲፱. ወይከድኖሙ ለሮም ኀፍረት በቅድመ ኢትዮጵያ ኀበ ዘወረደ ሎሙ መንፈስ ቅዱስ ዲበ ምሥዋዒሆሙ ወይትፌሣሕ ንጉሠ ኢትዮጵያ ። ወይዌውዕ በቃለ ይባቤ ምስለ ሕዘቢሁ ። ወሊቀ ጳጳሳት ዘእለእስክንድርያኒ ምስለ ኤጲስ ቆጶሳተ ግብፅ ወምስለ ኵሉ መምህራኒሆሙ ይትፌሥሑ በሙ ለሰብአ ኢትዮጵያ እስመ በቃለ መጻሕፍቲሆሙ ሥሙራን ኮነ ሥምረተ እግዚአብሔር ።

፲፮. የሮሜም ንጉሥ ከቍስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳሳት ጋራ የእኛ ሃይማኖት ይሻላል ይላል ። ዳግመኛም የኢትዮጵያ ንጉሥ ከእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ጋራ አንድ ኾኖ የእኛ ሃይማ ኖት ትሻላለች ያማረችም ናት ። እናንተ የሮሜ ሰዎች ትሰብ እትን ከመለኮት ከፈላችሁ ። የማይከፈለውን ከፈላችሁት የማይለየውንም እርሱን ለያችሁት ይላቸዋል ። የመጻሕፍትን ቃልም በመጥቀስ ክርክር ይበዛል ።

፲፯. ለኢትዮጵያ ሰዎች የብሉይ መጻሕፍቶቻቸው ትው ፊት ንግሥተ አዜብ ከኢየሩሳሌም በወጣች ጊዜ ነውና ። የሐዲሳት መጻሕፍቶቻቸውም ትውፊት በዘጠኙ የሮሜ ቅዱሳን መምጣት ጊዜ ነውና ። ነቢይ ኢሳይያስ ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ ላለች መጻሕፍትን ለምትልክ ለዚያች ሀገር ወሮላት እንዳለ የኢትዮጵያ ሊቃውንትም የሮሜ ሊቃውንትን ያሸንፏቸዋል ። የኢትዮጵያውያን መጻሕፍት ከዓለም ዳርቻዎች ኹሉ መጻሕፍት ይልቅ በልጠዋልና።

$$\text{ኢሳ} = ፲፰ + ፩$$

፲፰. ከዚኽም በኋላ ሮማውያን በመሠዊያቸው ላይ መንፈስ ቅዱስ በወረደላቸው በኢትዮጵያውያን ማሸነፍ እጀግ ያፍራሉ ። የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳትም ከግብፅ ኢጲስቆጳሳትና ከመምህራኖቻቸው ኹሉ ጋራ በኢትዮጵያ ሰዎች ደስ ይሰኙባቸዋል ። የእግዚአብሔር ፈቃድ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በአሉ የተወደዱ መጻሕፍቶቻቸው ውስጥ እውነተኛ ቃል እንዲ ገኝ አድርጎልና

፲፱. ወበእንተዝ ይቤ ነቢይ ኢሳይያስ ይትሜክሑ ግብፅ በኢትዮጵያ እስመ ሰብአ ግብፅ ወኢትዮጵያ ሱቱፋነ ሃይማኖት ወነቢራነ ክህነት እመንቱ ። ወእምዝ ይሰብሱ ነፍረተ መንሣረ ሰብአ ሮሜ ምስለ ሊቀ ጳጳሳቲሆሙ ወምስለ ንጉሦሙ ምስለ ኤጲስ ቆጳሳቲሆሙ ወምስለ ኩሉ ተዐይነ ማኅበሮሙ ።

፳. ወበእንተዝ ይቤ ዳዊት ነቢይ ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ ። ወጸላዕቱሂ ሐመደ ይቀምሑ ። አማንኬ ይገንዩ ኢትዮጵያ በእንተ ዘከፈሎሙ መዊዐ በቃለ መጻሕፍቲሆሙ ከመ ያስተንፍርምሙ ለዐበይተ ሮሜ ። አማንኬ ዘይቤ ወጸላዕቱሂ ሐመደ ይቀምሑ ገዚ በእንተ ንሣረ ሰብክቶሙ ለመለክአውያን

፳፩. ወመለክአውያንሰ ብሂል ሰብአ ንጉሥ ብሂል ። ወአኮ እመንቱ ሰብአ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ ነበ ሠምረ መርቅያን ንጉሥ ክነ ተመይጠቶሙ በእንተ ፍርሐተ ኵነኔ ወስደት ። ወበእንተዝ ተሰምዩ ንጉሣውያነ ወአኮ ክርስቶሳውያን እስመ መለክ ብሂል ንጉሥ ብሂል በልሳነ ዐረብ ወስመ ሃይማ ኖቶሙ ያዐውቅ ካህዶሙ እስመ አድለዉ ለንጉሥ እምያድልዉ ለእግዚአብሔር አምላኮሙ ።

፳፪. ወንትመየጥኬ ነበ ነገረ ዜናሆሙ ለንጉሠ ሮም ወለሊቀ ጳጳሳት ዘቀስጥንጥንያ ወለኩሉ ማኅበረ ተዐይነኒሆሙ ዘከመ ይኤሥሉ ወይትመየጡ እምሃይማኖቶሙ ርኵስት ሶበ ይፈእዩ ርደተ መንፈስ ቅዱስ ዲበ ምሥዋዕሁ ለሊቀ ጳጳሳት ዘእለእስክንድርያ ወይዌርዉ መጻሕፍቲሆሙ ውስተ ቀላየ ባሕር ዘውእቱ መጻሕፍተ ሐሰት ዘእስተንፈስ ሰይጣን ውስተ አፉሆሙ ወዓዲ ይረግምዎ ለውእቱ ልዮን አቡሆሙ ርጉም ዘመሀርሙ ዕልወተ

፻፱. ስለዚኽም ነገር ነቢይ ኢሳይያስ አስቀድሞ ግብጻውያን በኢትዮጵያውያን ይመካሉ አለ ። የግብጽና የኢትዮጵያ ሰዎች በሃይማኖት አንድ በክህነትም የሚተባበሩ ናቸውና የርሙ ሰዎችም ከሊቀጳጳሳቸውና ከንጉሣቸው ጋራ ከኤጲስቆጳሳቶቻቸውና ከተሰበሰቡትም ኹሉ ጋራ ነፍረትንና ነሣርን ይሰብሳሉ ።

፻፲. ነቢይ ዳዊት ኢትዮጵያውያን በፊቱ ይገዛሉ ። በእውነትም ጠላቶቹም አመድን ይቅማሉ ሲልም ኢትዮጵያውያን የርሜን ሊቃውንት በመጻሕፍት ቃል ያሳፍሯቸው ዘንድ ማሸነ ፍን አድሏቸዋልና ። በእውነትም ጠላቱቹ አመድን ይቅማሉ ያለው ስለእነዚያ መለካውያን የሰብክታቸው ጉስቍልና ነው ።

፻፲፩. መለካውያን ማለት የንጉሥ ሰዎች ማለት ነው እንጂ የኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች ማለት አይደለም ። ቅጣትና ስደትን ስለ መፍራት ንጉሥ መርቅያን ወደ ወደደው ተመልሰ ዋልና ። ስለዚህም ንጉሣውያን ተባሉ ። ክርስቶሳውያን ግን አይደሉም ። መላኪ ማለት በዐረብ ቋንቋ ንጉሥ ማለት ነው የሃይማኖታቸው ስያሜ ክህደታቸውን ያሳውቃልና ለአምላካቸው እግዚአብሔርም ከማያደሉ ይልቅ ለንጉሥ አድልተዋልና ።

፻፲፪. ወደሮም ንጉሥና ወደ ቍስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳሳት ወደጉባኤቻቸው የአንድነት ነገርም እንመለስና ሮማውያን ንሥሓ ገብተው ከረከሰች ሃይማኖታቸው በሚመለሱበት ምክንያት በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት መሠዊያ ላይ የመንፈስ ቅዱስን መውረድ በአዩ ጊዜ ሰይጣን በአፉ እና ያለባቸውን የሐሰት መጻሕፍቶቻቸውን ወደ ጥልቅ ባሕር ይወረውራሉ ። ዳግመኛም ክህደትን ያስተማራቸ ያ ርኵም አባታቸው ልዮንን መልሰው ይረግሙታል ።

፹፫. ወእምዝ ይክውን ፍትር ወስንዕ ወሰላም ማዕከለ ንጉሥ ኢትዮጵያ ወማዕከለ ንጉሥ ሮም ። ወበተንሥኡ ይትኤ የል ንጉሥ ኢትዮጵያ ዘውእቱሂ ቴምድሮስ ትውልደ አንበሳ ።

፹፬. ወይገብእ ምኵናነ ኢየሩሳሌም ኀበ ንጉሥ ሮም ወዘምኵናነ ምስር ወግብፅ ኀበ ንጉሥ ኢትዮጵያ ። ወበውእቱ መዋዕል ይክውን ብዙኀ ቀትል በውስተ ሐይቀ ባሕር ወበውስተ ብሔርሂ ወምህላዉ ለሰብእ በበገጾም ወበበውስተ ጾላፅት ። ወጽሉዓን እለ ይነብሩ በውስተ በድው ይመጽኡ ። ወይበ ውኡ ውስተ ቤተ መቅደስ ወይቀትሉ በዙርኖሙ ። ወአብያተ ክርስቲያናት እስከ የዐያ ። ወይበልዑ አራዊት ሥጋ ሰብእ ። ወትትሀወክ ሀገር ።

፹፭. ወክመ ተነበዩ ቅድመ እሎንቱ ጠቢባን እምቅድመ ምጽአቱ ለውእቱ ንጉሥ ይክውን ፀብዕ ወሀውክ ረኃብ ወተሰደ ውስተ ደስያቲሆሙ ለሮም ወለሶርያ ወለኢየሩሳሌም ። ወይትመ ዘበራ ሐይመታቲ ፍጥረት ምስለ ድንጋጋተ ባሕር ። ወይክውን በሳምናይ ዘመን ድንጋጌ ወሀውክ ባሕቲቱ ። መአብያተ ክርስቲያናትኒ ይትመዘበራ በበአሉ ። ወይማስኑ ድንጋጋት ወይክውን ድንጋጌ ወሀውክ ዲበ አጋእዝተ ደስያት ። ወሚጢዋን ይበዝኑ ። ወይትንሥል ማዕከለ ሮም ወአፍርንጊ ። ወይበዝን ፀብዕ በክሉ ።

፹፮. ወበውእቱ መዋዕል ወበኀበ ሰብአ ኵሉ በሐውርት በሐሰት ወበዐመፃ ይነብሩ ። ንብር ይነብር ። ወሊቅ ይሠርሕ ዓመት ትነብር ። ወአግዝእት ተሐርዕ ። አግብርት ይትሜሰልጦሙ

፳፫. ከዚኽም በኋላ ፍትርና ስምምነት ሰላምም በኢትዮጵያ ንጉሥና በሮም ንጉሥ መኻል ይኾናል ። የኢትዮጵያው ንጉሥም በነይሉ እጅግ የጸና ይኾናል ። ይኽውም የኢትዮጵያ ንጉሥ የተባለ ቱምድሮስ የተሰኘ አንበሳ የአንበሳ ደቦል ነው ።

፳፬. የኢየሩሳሌምም ግዛት ወደ ሮም ንጉሥ ይመለሳል የምስርና የግብጽ ግዛትም ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ይመለሳሉ ። በዚያ ዘመንም በባሕር ወደብ ዳርቻ በእየብሔሩም ጦርነት እልቂት ስደት ይኾናል ። የሰውም ኹሉ ኑሮው በእየበረኻ ውና በእየዋሻው ይኾናል በባሕር አካባቢ የሚኖሩ ርኩሳን ሰዎችም ወደ ቤተ መቅደስ ይገባሉ ። አብያተ ክርስቲያንንም ያቃጥ ላሉ አራዊትም የሰውን ሥጋ ይበላሉ ። ሀገርም ትታወክለች ይላል ።

፳፭. እሊያ ጠቢባን አስቀድመው እንደአዩትም ከንጉሡ መምጣት በፊት በሮምና በሶርያና በኢየሩሳሌምም በደሴት አገሮች በሌሎችም ጦርነትና ስደት ራብም ይኾናል ። ብዙ ሰዎችም በባሕር ዳርቻዎች ያልቃሉ ። በስምንተኛው ዘመን ብዙ ችግርና ድንጋጤ ብቻ ይኾናል ። አብያተ ክርስቲያናት በእየአው ራጃዎቹ ይፈርሳሉ ። የባሕር ዳርቾች ይጠፋሉ ። በደሴቶች ሰዎች ላይ ድንጋጤና ሽብር ይነግሣል ። ሰዎችም ይማረካሉ ፍርሐትና ሽብርም ይበዛል ። በሮምና አፍርንጊ መካከልም መንገድ ይታጣል ። በኹሉም ሥፍራ ጦርነት ይኾናል ።

፳፮. በዚያ ዘመን በእየአገሩ ያሉ ከአሉ ሰዎች በዓመፃና በውሸት የሚኖሩ ይበዛሉ ። በዚያን ዘመን አገልጋይ ይከብራል ታላቅ ይሠራል ይደክማል ። አገልጋይ ትከብራለች ። እመቤት

ለአጋእዝት ። ወዘኢይትአመሩ አበዊሆሙ ወእሞሙ ይክውኑ ሥዩማነ ውስተ ኵሉ በሐውርት ። ወኢያእምርያን ይክብሩ መስሞሙ ዲበ ሥልጣኖሙ ነዊኅ ። ወእምኔሆሙ ይበ ዝኅ ኃጢአት ። ወትበዝኅ ዐመፃ ። ወትሴከሶ ጽድቅ ።

፳፯. ወበውእቱ መዋዕል ይበዝኑ ሐሳውያን ካህናት ወይክውኑ ጊጉያነ ወዐሳብያነ ሕልያን ። ወየሐውሩ በፍኖተ ኃጢአት ወይክውኑ መፍቀርያነ መብልዕ ወመስቴ ። ወኢይቀብሩ ሙታነ ጥቀ ወኢይትነሥኡ ለጸሎት ። ወይትዔበዩ ላዕለ ሕዝብ በእንተ ዘተውህበቶሙ ቃል ። ወሃይማኖት ትሴስል እምኔሆሙ ወእሙንቱ ይትነፈሩ በምግባራቲሆሙ በቅድመ መኰንነ ጽድቅ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በደኃሪ መዋዕል ። ስምዑኬ ቃሎሙ ባሕቱሂ ኢትግበሩ ዘከመ ይገብሩ እሙንቱ ።

፳፰. ወይቤ እግዚአብሔር አነሥእ ዕንለ አንበሳ ዘተን ሥአቱኬ ከመ ዘንቃህ እምንዋም ። ወይሰድዶሙ ለዅሎሙ ነገሥት እስመ ሎቱ ተውህበቶ ሥላጤ ኀይል ።

፳፱. ወቅድመ ውእቱ መዋዕል ሶርያ ትትመዘበር ። ወሰብእ የኀልቅ ይትፈጸም ቃለ ዳንኤል ነቢይ ዘይቤ ገዳም ትፃሙ እምፈላስ ያን እለ የኀድሩ ውስቴታ ። ወአልቦ እለ ይነ ብሩ ውስተ አድባር ዘእንበለ ዘያንጐግጒ ። ወዝ ኵሉ በሳምናይ ዘመን ይከውን ።

፴. ወበውእቱ ዘመን አበው ይክህዱ ውሉዶሙ ። ወውሉድ ይክሀዱ አበዊሆሙ ። ወይትነሥኡ አግብርት ወይቀትሉ አጋእዝቲሆሙ ወይነሥኡ ምኵናኒሆሙ ። ወዘኢይትዐወቅ ይመልክ ብሔረ ወዐባይ ሀገር እንተ ምሥራቅ ይትነሣእ ላዕሌሃ ቀትል ሠሉሰ

ትፈጫለች ። አገልጋዮች ጌቶቻቸውን ይመስሏቸዋል ። ትውልዳቸው የማይታወቁ የነበሩ ሰዎች በእየሀገሩ ኹሉ ይሾማሉ ። ያልተማሩም ስማቸው በሥልጣናቸው ላይ ይገንናል ከእነሩሱም የተነሣ ነጢአትና ዓመፃ ትበዛለች ። እውነትም ትጠፋለች ።

፳፮. በዚያ ወራት ሐሰተኞች ካህናት ይበዛሉ ። በደለኞችና ጕበኞች ኾነው በኃጢአት ጎዳናም ይሔዳሉ ። መብልንና መጠጥን የሚወዱ ይኾናሉ ። ስለተሰጣቸው ሥልጣነ ክህነት ብቻ በሕዝቡ ላይ ይታጀራሉ እንጂ የሞቱትን አይቀብሩም ። ሰጸሎትም አይተጉም ። ከእነርሱም የተነሣ ሃይማኖት ትጐድላለች እነርሱም በኃለኛው ዘመን በእውነተኛ ፈራጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት በሥራቸው ያፍራሉ ። የሚሏችሁን ሰሙ እንጂ እነርሱ እንደሚሠሩት ያለ ክፋትን አትሥሩ ።

፳፯. እግዚአብሔርም አነሣሱ ከእንቅልፍ እንደ መነሣት ያለ የእንበሳ ደቦልን አነሣለሁ ። ነገሥታትን ኹሉ አሳድዶ ያጠፋቸዋል ። ለእርሱ ሥልጣንን ሰጥቼዋለሁና ይላል ።

፳፱. ከዚያ ዘመን አስቀድሞም ሶርያ ትፈርሳለች ። ሰውም ያልቃል በውስጧ ከሚኖሩ ስደተኞች የተነሣ ገዳም ትጨነቃለች ብሎ ነቢይ ዳንኤል የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ ከሚቅበዘበዙ በቀር በከተሞች ውስጥ የሚኖሩ አይገኙም ። ይኽ ኹሉ በስምንተኛው ዘመን ይኾናል ።

፴. በዚያ ዘመን አባቶች ልጆቻቸውን ፤ ልጆችም አባቶቻቸውን ይክዳሉ ። አገልጋዮችም ጌቶቻቸውን ገድለው ግዛቶቻቸውን ይወስዳሉ ። የማይታወቅ ኃይል አገርን ይገዛል በምሥራቅ በኩል ባለች ታላቅ አገር ላይ ለሦስት ዓመታት ጦርነት ይነሣል

ዓመታቲ ። ወአልቦ ዘይተርፍ ላዕሌሃ ዘእንበለ ውኑዳን ነሣ ሕያን በቅድመ እግዚአብሔር ኀር ርኑቀ መዓት ውብዙኀ ምሕረት ።

፴፩. ወበውእቱ መዋዕል ካህናት ወሕዝብ ይስእሉ ኀበ አምላኮሙ እግዚአብሔር ወይግዕሩ ። ወእምብዝኀ ኀጢአቶሙኢይመይጥ እግዚአብሔር ገጸ ኀቤሆሙ ። ወኢይሰምዖሙ ጸሎቶሙ ወትበዝኅ እኪት በውእቱ ዘመን እምቀዳሚ እስከ ደኀሪ ። ወይክውን ምንዳቤ ብዙኅ እስከ ይብልዎሙ ሕያዋን ለሙታን ብፁዓን አንትሙ ።

፴፪. ወበውእቱ መዋዕል ይመጽእ ቴዎድሮስ ዕንለ አንበሳ እምሥራቅ ወይትሐነጻ አህጉር እለ መዝበራ ኵሎን በዲበ ምድር ። ወታቦት ትትሐነፅ ። ወይክውን ውስተ ኵሉ ዓለም በመዋዕሊሁ ጽጋብ ። ወበየኀልፉ ሕያዋን ኀበ መቃብረ እለ ቀደሙ ወሞቱ አዝማዲሆሙ ወይብልዎሙ አንትሙ እለ አዕረፍክሙ በመዋዕለ ኀዘን ምንትኬ ይእዜ እመ ትትነሥኡ ወትርአዩ ፍሥሓ ወሐሤተ ወጽጋበ ኀበ ይእዜ ሀሎን ንሕነ ።

፴፫. ወይክውን መንግሥቱ ለውእቱ ብእሲ ኀር ንጉሥ ቴዎድሮስ ዘተሰምየ አንበሳ ዕንለ አንበሳ ፯ ዓመት ። ወእምድኅረ ፈጸመ ነጊረ ከመዝ ኵሎ ዘንተ ትንቢተ ይቤላ ለእሙ ሰላም ለኪ አ እምየ ማርታ ። ወዘንተ ብሂሎ ሖረ እምኔሃ ። ወይእዜኒ ይትባረክ እግዚአብሔር ዘወሀቦ ዘንተ ኵሎ መንፈሰ ትንቢት ለውእቱ ቅዱስ ማር ፈቅሮር ለማዕት በከመ አቅዲሙ ነገረ በልሳነ ቅዱስ መጽሐፍ ዘይቤ ብነ ዓዲ ዘእምዝኒ ይቀድም


መዓቱ በራቀ ምሕረቱ በበዛ ቸር አምላካቸው እግዚአብሔር ፊት ንሥሓ ከሚገቡ በቀር የሚተርፍም የለም ::

፴፩. በዚያ ዘመን ካህናትና ሕዝቡ ወደአምላክቸው እግዚአብሔር በጭንቅ ይለምናሉ :: ነገር ግን ከኃጢአታቸውየተነሣ እርሱ እግዚአብሔር ገጸ ምሕረቱን ይመልስባቸዋል :: ጸሎታቸውንም አይሰማቸውም :: በዚያ ዘመን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ክፋት ትበዛለች :: የሞቱትን ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናችሁ እስኪሏቸው ድረስ ብዙ ችግርና ኀዘን ይደርሳል ::

፴፪. በዚያን ዘመን የአንበሳ ደቦል የተባለ ደግኛ ንጉሥ ቴዎድሮስ ከምሥራቅ ይመጣል :: በዚያ ዘመን በምድር ላይ የፈረሱ ሀገሮች ይታነፃሉ :: ቤተ መቅደስ ትታነፃለች :: ታቦት ትተከላለች :: በዓለም ኹሉ በዘመኑ ጥጋብ ይኾናል ::በዚያን ዘመን ሕያዋንም አስቀድመው ወደዐረፉት ወገኖቻቸው መቃብር ሒደው በዚያ የኀዘን ዘመን የዐረፋችሁ እናንተ ወገኖቻችን እኛ አሁን ባለንበት ያለውን ተድላ ደስታና ጥጋብን ታዩ ዘንድ ዛሬ ምነው ብትነሡ ይሏቸዋል ::

፴፫. የዚኽም የአንበሳ ደቦል የተባለ ደግኛ ንጉሥ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥቱ አርባ ዘመን ነው :: ይኽንን ኹሉ ትንቢት ተናግሮ ከፈጸመ በኋላ እናቱን እናቱ ማርታ ሆይ ሰላምና ፍቅር ከአንቺ ጋራ ይኹን አላት :: ይኽንንም ብሏት ከእርሷ ተሠወረ :: ከዚኽም የሚበልጥ ገና ይኽንንም የሚገልጥ የትንቢት ቃል አለን ተብሎ አስቀድሞ በቅዱስ መጽሐፍ እንደ በት እንደ ተነገረ አሁንም ይኽንን መንፈሰ ትንቢት ኹሉ በሰማዕት ቅዱስ ፊቅጦር ላይ ያሳደረ እግዚአብሔር ይመስገን :: ስለተጋድሎው

ቃለ ትንቢት ዘያዐውቅ ዘንተ ። ጸሎቱሰ መበረከቱ ለውእቱ ቅዱስ ማር ፈቅሮር ዘኮነ ሎቱ ኵልቄ ሰማዕትናሁ እምኵሉመ ቅዱሳን ሰማዕታት አበው በእንተ ጽንዐ ፃማሁ ምስለ.....ለዓለም መለዓለመ ዓለም አሜን ።



ጽናት የለማዕትነት ቊጥሩ ከኹላቸው ቅዱሳን ሰማዕታት ጋራ የተደመረ የተወደደ ቅዱስ ፊቅጦር ጸሎቱና በረከቱም ከ.....ጋራ ይኹን ለዘለዓለሙ አሜን ::

